# የእርስዎን DeLonghi (PAC EL112 CST) መጠቀም

## እንዴት እንደሚሰራ አጭር መመርያ

**የመክፈቻ እና የማጥፊያ ቁልፍ (Swing button)**

ይህን ቁልፍ ወደ ላይ እና ወደ ታች በማድረግ የአየር ማቀዝቀዣውን ለመጀመር ወይም ለማቆም ይጠቀሙ።

**ማርገብገብ ፍጥነት**

( ፨ ) ዝቅተኛ
(( ፨ )) መካከለኛ
((( ፨ ))) ከፍተኛ
AUTO አውቶማቲክ


**ወደኋላ የሚቆጥር ሰአት ቆጣሪ**

የአየር ማቀዝቀዣው በራሱ ጊዜ እንዲያቆም ይህን ቁልፍ ይጫኑ። ሰዓቱን ለማስተካከል የመቀነስ/መጨመር ቁልፎችን ይጠቀሙ።

**የሁኔታ ቁልፍ (Mode**

ከሚከተሉት ለመምረጥ ይህንን ይጠቀሙ:-

- ✳ የአየር ሙቀት መመጠኛ
- 💧 እርጥበትን ከአየር ማስወገድ
- ✤ ማርገብገብ




**አብራ እና አጥፋ ቁልፍ**

ለማብራት ወይም ለማጥፋት ይጠቀሙ።

**ቀንስ / ጨምር ቁልፍ**

ሙቀትን ወይም ሰዓት ቆጣሪን ለመቀየር ይህንን ይጠቀሙ።

## ስለ አየር ማቀዝቀዣ ምክሮች እና ብልሃቶች

- ቤትዎን ለማቀዝቀዝ እና ጥሩ ቅዝቃዜ ለማግኘት የአየር ማቀዝቀዣ ማቀናጃውን (mode) ይጠቀሙ።
- የአየር ማቀዝቀዣው ደልዳላ መሬት ላይ መቆሙን ያረጋግጡ።
- ለምቾት እና ለፍቱን አጠቃቀም፣ የአየር ማቀዝቀዣዎን ወደ 24-26° ያቀናጁ። የዝቅተኛ የሙቀት መጠን ቅንጅቶች የበለጠ ኃይል ይጠቀማሉ እና የበለጠ ያስከፍላሉ።
- የአየር ማስገቢያውን ወይም የመውጫ ሽፋን አይዝጉ።
- የአየር ማቀዝቀዣውን ሲጠቀሙ መስኮቶችን ይዝጉ።
- መጋረጃዎችን እና የመስኮት መከለያዎችን በመዝጋት ቀን-ቀን በቤት ውስጥ ፀሐይን ያግዱ።
- ከባድ ነገሮችን በዚህ ማሽን ላይ አታስቀምጡ።
- ሃይልን እና ገንዘብን ለመቆጠብ የአየር ማቀዝቀዣዎን ማቀናጃ ቀኑን ሙሉ እንደሁኔታው ያስተካክሉት:-
  - በሞቃት ቀናት ቤትዎን አስቀድመው ያቀዘቅዙ።
  - በጣም ሞቃታማ በሆነ ቀን፣ የአየር ማቀዝቀዣውን ከፍ ባለ ሙቀት ላይ ያድርጉ።

## ጥያቄ አልዎት?

HighRiseCooling@homes.vic.gov.au

1800 519 721

www.homes.vic.gov.au/cooling-our-high-rise-towers

በቪክቶሪያ መንግስት የተፈቀደ እና የታተመ፣ 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria፣ ሆምስ ቪክቶሪያ፣ መጋቢት 2025።
በFinsbury Green, Melbourne Victoria, 3000 (HV004225) የሚተዳደር ህትመት


# የአየር ማቀዝቀዣዎን ማንቀሳቀስ


**ከአንድ በላይ ዋና ቀዳዳ** ካልዎት፣ የአየር ማቀዝቀዣዎን በሁለቱም ቀዳዳዎች መካከል ማንቀሳቀስ ይችላሉ። ይህንን ለማድረግ፡-


1. ቱቦውን ከዋናው ቀዳዳ ለማስለቀቅ የአየር ማናፈሻ ቱቦን ወደ ግራ ያዙሩት።

2. የአየር ማቀዝቀዣውን ወደሚፈልጉት ቦታ ያንቀሳቅሱት።


3. የአየር ማናፈሻ ቱቦውን ወደ ቀኝ አዙረው ወደ ዋናው ቀዳዳ ያጣብቁት።





**የአየር ማናፈሻ ቱቦዎ ከማቀዝቀዣው** ከወጣ፣ በአየር ማቀዝቀዣው ላይ ባለው ቀዳዳ ውስጥ ቱቦውን ወደ ቀኝ በማዞር እንደገና ያያይዙት።




## የጥገና ጉዳዮች፡-

**በአየር ማቀዝቀዣዎ ላይ ሊታዩ ስለሚችሉ ማናቸውም ብልሽቶች ወይም የጥገና ጉዳዮች፣ የቤቶች የስልክ ጥሪ ማዕከልን በ 13 11 72 ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የቤቶች ቢሮ (housing office) ያነጋግሩ።**


# ጥገና

## ማጣሪያውን ማጽዳት

ማጣሪያውን በመደበኛነት ማጽዳት ማለት ማቀዝቀዣው በተሻለ ሁኔታ ይሰራል እና ለረጅም ጊዜ ይቆያል ማለት ነው።

ለማጽዳት ቫክዩም ወይም ሙቅ ውሃ (ከ 40 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች) ይጠቀሙ።

እንደገና ከማስገባትዎ በፊት ሙሉ በሙሉ እንዲደርቅ ያድርጉት።




# በጣም የተለመዱ የስህተት መልዕክቶች

| ከሆነ... ታይቷል |
| --- |
| HL ⚠ |
| "ከፍተኛ ደረጃ" (የውስጥ ትሪ ሙሉ) |
| **..ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ?** |

### ከማሽኑ ውስጥ ውሃ ማፍሰስ

- በማሽኑ ስር አንድ ባልዲ ወይም ትሪ ያስቀምጡ።
- ክዳኑን ይንቀሉት እና ያስወግዱት።
- ውሃውን ያፍስሱ።
- ክዳኑን መልሰው ይክደኑ።
- ማጣሪያውን ያጽዱ።



| ከሆነ... ታይቷል |
| --- |
| E1 ⚠ |
| "የግንኙነት ውድቀት" (የውስጥ ግንኙነት ጉዳይ) |
| **..ምን ማድረግ ነው የሚገባኝ?** |

### የግንኙነት ውድቀት

1. ለ 15 ሰከንድ ማሽኑን ከግድግዳው ሶኬት ይንቀሉ።
2. መልሰው ይሰኩት እና ያብሩ።
3. ችግሩ ካልተፈታ፣ የጥገና ክፍሉን ያነጋግሩ።